# እርቅ ፣እምነትና ሽምግልና

ከዳዊት ፍሬው

ኢትዮጵያ አገራችን ካሏት ትላልቅ በሕላዊ እሴቶች አንዱ እርቅ ነው። እርቅ በግለሰቦች፣ በቡድኖች፣ ሰፋ ሲልም በአገሮች መካከል የተፈጠሩትን ችግሮች ተረድቶ ችግሮቹን ለመፍታት ወይም የተጣሉትን ለማስማማት የሚዳረግ ጥረት ነው። እንደ ጉዳዩ ዓይነት የሚመደቡ ብዙ የእርቅ ዓይነቶች አሉ። እምነት ደግሞ በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል የተወሰኑ ዓላማዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈጸም ቃል ኪዳን ወይም ትስስር ነው። የእምነት ዓይነቶችም ብዙ ናቸው። በተጣሉ ወገኖች መካካል እርቅ ለመፍጠር የሚደረገው ክንውን ሽምግልና ነው። በአገራችን ባሕል መሰረት እርቅን በተጣሉ ወገኖች መካካል ለመፍጠር የሚመረጡት ሽማግሌዎች ናቸው።ሽማግሌዎቹ በተጣሉት ወገኖች አካባቢ እውነት አይተው ያስማማሉ ተብለው ተቀባይነት ይኖራቸዋል። አንዳንዴም ከሁለቱም ወገኖች እኩል ቁጥር ያላቸው ሰዎች ተመርጠው ሰብሳቢ የሚመርጡበት ሁኔታ አለ። በተለይ ጉዳዩ ከፍርድ ቤት በሽምግልና እንዲያልቅ የሚዳረግ ከሆነ ሰብሳቢው ከፍርድ ቤት ይወከላል። ከተጣሉት ወገኖች አንዱ ሽማግሌ ሆኖ በሚሰየመው ሰው ላይ እምነት ከሌለው ሽማግሌው ሽምጋይ ሊሆን አይችልም። ሌላ ሁለቱም የሚያምኑት ሰው ፍለጋ ይካሔዳል። ሽማግሌዎች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። የሽምግልና መሰረቱ ደግሞ እውነትን ለይቶ በማወቅ ለተበዳዩ ወገን ፍርድ በመስጠት ማስታረቅ መቻል ነው። አለበለዚያ ሽምግልናው ሽንገላ ሆኖ ይቀራል። በአገራችን በአንዳንድ አካባቢዎች የግድያ ወንጀል እንኳን ሲፈጸም በዳዩ ተበዳዩን እግሩ ላይ ወድቆ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ እንዲጠይቅና አስፈላጊውን ካሳ ክፍሎ ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ያደርጋሉ። ጉዳዩም ከሁለቱም ወገን እንደገና እንዳይነሳና ወደ ፍርድ ቤት እንዳይሄድ ሲፈልጉ በመሀላ የሚያስማሙበት ወቅትም አለ።

ይህችን አጭር ጽሑፍ እንዲሞነጫጭር ምክንያት የሆነኝ ከሰሞኑ ኢሕአፓን አስመልክቶ እርቅ ሊወርድ ነው፤ ሽማግሌዎች በመኻል ገብተዋል ተብሎ እየተወራ ያለውን ጉዳይና ከዚሁ ጋር ተያይዞ እየተደረጉ ያሉ ጥፋቶችን በሚመለከት ይሆናል። እኔ አንደ አንድ ኢትዮጵያዊ የኢሕአፓን ጥንካሬ እሻለሁ፣ ለአገራችንና ለሕዝባችን ካደረገውና አሁንም እያደረገ ካለው ትግልና አስተዋጽዖ አንጻር ድርጅቱ በሁሉም መልክ መደገፍ እንዳለበትም እምነቴ ነው። የድርጅቱን እንቅስቃሴና በሁሉም አቅጣጫ በድርጅቱ ላይ የሚደረገውንም ጥቃቶች እከታተላለሁ ። የድርጅቱን ድረገጽ፣ ሬዲዮ ጣቢያዎች ፣ የጽሁፍ መረጃዎችን በደንብ አይቻለሁ። ይህን መሰረት በማድረግ እርቅ እናድርግ፣ ሽምግሌዎች ጉዳዩን እንዲያዩ ልከናል የሚሉ ቡድኖች ምን ሲያደርጉና እያደረጉ እንዳሉ በጥቂቱ ከዚህ በታች አቀርብና መፍትሔውንም አስከትላለሁ፡-

- የድርጅቱ ውሳኔ ሰጭ የሆነውን ጠቅላላ ጉባኤ ሀሳባቸውን ሳያቀርቡ ረግጦ መውጣት፣
- በድርጅቱ ላይ አንጃ ፈጥረው ተለጣፊ ድርጅት ኢሕአፓዲ( ዲ = ዲሞክራሲያዊ) ማቋቋም፣
- የድርጅቱን ዓርማና ልሳን ያለ አግባብ በመጠቀም የኢትዮጵያን ሕዝብ ውዥንብር ውስጥ መክተት ፣
- ለድርጅቱ ደንብና ዲስፕሊን ተገዢ ባለመሆን የሚፈልግባቸውን ግዴታ በአግባቡ አለመወጣት፣
- በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ፣
- ድርጅቱ በሕዝብ ውስጥ ያለውን ተደማጭነት ለማሳጣትና ሕዝብን ውዥንብር ውስጥ ለመክተት እርማት እንቅስቃሴ፣ ኢሕአፓ ትንሳኤ ወዘተ... በማለት ጸረ-ድርጅት ሥራ ማካሄድ፣

- ከድርጅቱ ጠላቶችና የድርጅቱን ውድቀት ከሚመኙ መገናኛ ብዙኃን ጋር በመተባበር ዘርፈ ብዙ ጥቃት በድርጅቱ ላይ መፈጸምና በመፈጸም ላይ መገኘት፣
- ድርጅቱን ከደው፣ አጥቅተው፣ አሁን ለወያኔ እየሰሩ ያሉትን ጭምር ቀድሞ የኢሕአፓ አባል የነበራችሁ ሁሉ በሚል ምክንያት( በድርጅቱና በሕዝብ ላይ ጥቃት የፈጸሙትን እና አቶ ታምራት ላይኔ፣ በረከት ስምዖን፣ መላኩ ተገኝ፣ ክፍሉ ታደሰ፣ ተፈራ ዋሉዋ፣ አዲሱ ለገሰ፣ሌሎች አንጃ ፈጣሪዎችን ይጨምራል) በኢሕአፓ ጉዳይ ላይ ተሰብሰቡ የሚል ጥሪ ማቅረብ ፣
- የቀድሞ አባላትን በማሰባሰብ ሰበብ በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጥቃት ያደረሱ ግለሰቦችን ማሰባሰብና ደግም በድርጅቱ ውስጥ አንጃ እንዲፈጠር ማድረግ፣
- ዘሬ እርቅ እንፍጠር ባዮች ውስጥ የተወሰኑት ከወያኔ ደህንነት ኃላፊዎች ጋር ግንኙነት ፈጥረው መገኘት ፣
- ኢሕአፓዎች ሁሉም አንድ ናቸው እርቅ ፈጥረው በጋራ መሥራት አለባቸው ከሚሉት ውስጥ በተለይ በኢዲኃቅ ውስጥ የነበረውን የአመራር ቦታ በመጠቀም የወከለውን ድርጅት ኢሕአፓን ሳያሳውቅ ድርጅቱ ውስጥ ተሰግስጎ በነበረው የወያኔ ሰው አማካይነት ከወያኔ ኤምባሲ ፓስፖርት ወስዶ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ እንቅስቃሴ ያዳረገ ግለሰብ መገኘት፣
- ኢሕአፓ ዘር፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ አካባቢ ሳይለይ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ቤት መሆኑን ረስተው ጎጣኝነትን በማስፋፋት ላይ የሚገኙ ግለሰቦች መኖር ፣
- የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት የሆነውን ወያኔ ፤ በስሙ አንጥረው ወያኔ አንበል፣ ኢህአዴግ እንበለው ፣ ወያኔን ይቅርታ ጠይቀን አዲስ አበባ እንግባ ያሉ ግለሰቦች መገኘት፣
- ከዚህ በፊትም ሁሉን ነገር ትተን ኢሕአፓዴንም አክስመን እርቅ እንፈልጋለን በማለት ውስጥ ውስጡን በአባላት መካከል ወሬ ሲያናፍሱ ቆይተው የእርቅ ሳይሆን አባላትን ሊከፋፍል የሚችል መልዕክት የያዘ ደብዳቤ ለኢሕአፓ ጽ/ቤት በኢሕአፓዲ ሎጎ መላካቸው፣
- ነሐሴ 17 ቀን 2006 ዓ.ም( August 23 , 2014 ) 42ኛ ዓመት ምስረታ በዓሉን ለማክበር ኢሕአፓ ማስታወቂያ በሬዲዮና በድረገጾች ከአወጣ ሁለት ወራት ያህል መሆኑ እየታወቀ፣ የታጋይቱን የአበራሽ በርታን ስም በያዘ የመወያየ ክፍል (Paltalk room) ያው የለመደባቸው የኢሕአፓ ከፋፋይ ግለሰቦች ( ክፍሉ ታደሰ ኢሕአፓ በኢሕአፓነት መቀጠል የለበትም በማለት ከድርጅቱ የወጣና፣ ከወያኔ ጋር ተስማምቶ ለመሥራት የዜና አገልግሎት ድርጅት (Broadcasting Agency) ለመቋቋም ወደ አዲስ አበባ የሄደ ግለሰብ፣ ዶ/ር መላኩ ተገኝ ድርጅቱን ከ35 ዓመት በፊት ለቆ፣ ወያኔዎችን ደግፎ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ፓኖስ በሚል ስም የሚንቀሳቀስና በሽፋን ለምእራቡ የስለላ ተግባር የሚያካሂድ ድርጅት ሰራተኛ የነበረ ግለሰብ፣ --) እና ድርጅቶችን በመከፋፋል ወያኔንና የኢትዮጵያ ጠላቶችን የሚጠቅመውና በማይመለከተው ጉዳይ ጣልቃ እየገባ የኢሕአፓን ሕጋዊ ዓርማ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለአልባሌ ሥራው እየተጠቀመ ከሚገኘው የአበበ በለው ሬዲዮ ጣቢያ ጋር በመተባበር ነሐሴ 10 ቀን 2006 ዓ.ም እርቅ ያሉት ጉዳይ ሁኔታው ገና በውል ሳይታወቅ የኢሕአፓን 42ኛ ዓመት ምሥረታ በዓል አከበርን በሚል ሰበብ ሕዝብን ውዥንብር ውስጥ ለመክተትና ነሐሴ 17 ቀን 2006 ዓ.ም(August 23, 2014) የሚከበረውን የድርጅቱን በዓል ለማደናቀፍ እየሴሩ መገኘት፣
- ከደርጅቱ አንጃ ሆኖ የወጣው ቡድን ለሽምግልና ሳይዘጋጅ ቀርቶ ኢሕአፓዴ የሚሉትን ሕገወጥ ጸረ-ኢሕአፓ እንቅስቃሴ አቁመው ከድርጅቱና ከአባላቱ ጋር ጤናማ ግንኙነት መፍጠር ሲገባቸው ለእርቅ ሽማግሌ ልከን ነበር አምቢ አሉ በማለት በድጋሚ ከወያኔና ከድርጅቱ ጠላቶች ጋር በማበር ጸረ-ድርጅትና ከፋፋይ ከሆነው የአበበ በለው ሬዲዮ ጋር በመተባበር ሕዝብን ውዥንብር ውስጥ እየከተቱ መገኘት፣ ጥፋታቸውን ሳያምኑና ለጥፋት ተልዕኳቸው

የሚጠቀሙበትን የድርጅቱን ዓርማና ልሳን መጠቀም ሳያቆሙ ምን ዓይነት እርቅ ነው ሊኖር የሚችለው? እንደው ዝም ብሎ እኛ እርቅ ጠይቀን ነበር በማለት አምቢ ያለው ሌላ ወገን ነው ብሎ ለማስወራት ታስቦ ካልሆነ በስተቀር ። አሁን በተግባር ድብቅ አጀንዳው ግልፅ ሆኗል። ሩጫው ሲካሄድ የነበረው ለእርቅ ሳይሆን ማታለያ መሆኑ ተረጋገጠ። እርቅ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከሩት እውነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ጥፋተኛውን ለይቶ ሰላም እንዲወርድ የሚያደርግ ቅዱስ ክንዋኔ ነው። ከላይ በዘረዘርኩት ነጥቦች ግልፅ ሆኖ እንደሚታየው በኢሕአፓ ውስጥ ሆነን እርቅ ፈጥረን አብረን መስራት እንፈልጋለን በምትሉት ወገኖች አማካይነት በተፈጸመው ከፍተኛ ድርጅታዊ አስራር ጥሰት በድርጅቱ ውስጥ ባሉ አባላት መካከል የእምነትና የአቋም ልዩነት ተፈጥሯል። ወያኔን ጠላት አንበለው፣ ወያኔን ወያኔ በሚል ስም አንጥራ ፣ ኢሕአዴግ እንበለው በማለት ከፈጠራችሁት ልዩነት ሌላ ጓዳዊነትና የድርጅቱ ደንብ ተጥሶ የአመራር አባላት ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ ፣ ጠቅላላ ጉባኤን ረግጦ በመውጣት፣ ድርጅታዊ ምስጥሮች በመዝራትና ብተና በማካሄድ፣ አባላትን ጠላት እንዲያውቃቸው በማድረግ ባጠቃላይ ድርጅታዊ ግዴታዎችን በማሟላት በኩል ያችግሮች ተፈጥረዋል ። በመጀመሪያ እርቅ ለማውረድ  በአባላት መካከል እምነትን ሊፈጥሩ የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። የተፈጸመው ወንጀል ከባድ ነው። ስህተቱን ማረም ይጠበቃል። ሌሎች እንዲያምኑና እንዲቀርቡ ለማድረግ ፍላጎትና ቁርጠኛነቱ ካለ ኢሕአፓዲ የሚባለውን በኢሕአፓ ላይ ተለጣፊ የሆነውን ማክሰም፣ የድርጅቱን ዓርማና ልሳን አለመጠቀም፣ ለጠላት በርን ከፍቶ በየቦታው በድርጅቱ ላይ የሚደረገውን ሕገወጥ ልፍለፋ ማቆም፣ በመሃላችሁ ሆነው ድርጅቱን ለማጥቃት የሚንቀሳቀሱትን ልምድ ያላቸውን በታኞች መራቅና ማራቅ፣ የድርጅቱ ጠላት የነበሩትን ሁሉ ወደ ድርጅቱ ይምጡ የምትሉትን በታኝ እንቅስቃሴ ማቆም፣ ከድርጅቱ አመራረ ላይ ሆነው በተደጋጋሚ ድርጅቱን በትነው የሄዱትን ግለሰቦች የኢትዮጵያን ሕዝብና ድርጅቱን ይቅርታ ሳይጠይቁ ቦታ አለመስጠቱ የሚጠበቅ ይሆናል ። ያለዚያማ ኢሕአፓ ምኑ ድርጅት ሆነ? ለማንም በታኝ በሩ ክፍት ሆኖ በድርጅቱ፣ በትግሉና በአጠቃላይም በአገርና በሕዝብ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከባድ ነው።የአንጀው ቡዱን መሪ ማታ ሌሊት ጠፍቶ ሌሎች ጥቂቶች ደግሞ የድርጅቱን ልዩ ጉባኤው ረግጠው ቢሄዱም የቀሩት አብዛኞቹ ጉባኤተኞች ከድርጅቱ የተለዩት አባላት በማንኛውም ጊዜ ወደ ድርጅታቸው ኢሕአፓ መመለስ እንደሚችሉ መግለጫ ካወጡ ቆይቷል። መግለጫው ዛሬም ይሰራል። እድሉን በመጠቀም ወደ ድርጅቱ መመለስ መብታችሁ ነው። ከሌሎች በየአካባቢያችሁ ከሚገኙ ጓዶቻችሁ ጋር ቅርበት መፍጠር ፣ድርጅቱን መርዳት፣ ትብብርን ማጠናከር ከእናንተ ይጠበቃል። ለድርጅቱ ጠላቶች በሁሉም መልኩ ቀዳዳ አለመስጠት። ያንን ካዳረጋችሁ ለኢሕአፓዎች ሽማግሌ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ስተዋደዱ ተመልካቹን ሁሉ የምታስቀኑትን ያህል ስትጣሉም ከባዶች ናችሁ። ለዚህ ደግሞ ትልቁን ሚና የሚጫወተው የእምነት መሸርሸር ጉዳይ ነው። በእውነት ለድርጅታችሁ ጥንካሬ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበር፣ለአገሪቱ ሉአላዊነት፣ የተሰውት ጓዶቻችሁ ትተው ያላፉት አደራ ሁልጊዜ ትዝ ለሚላችሁ ቃልኪዳናችሁን እንደገና ማደስና እምነትን መፍጠር ከባድ የሚሆን አይመስለኝም። የለመደችሁበትና ያዳጋችሁበት ሂስና ግለሂስም አለ። ከዚህ ወጣ ሲባል ነው ችግር የሚፈጠረውና የተፈጠረውም።

ከሁሉ በፊት በልዩነቱ ለመጠቀም በውስጣችሁ የሚርመሰመሱትን የድርጅቱን ጠላቶች አውቆ መለየት ያስፈልጋል።

ለማስታረቅ ጥረት ለማድረግ የመጡትን ሽማግሌዎች በበኩሌ አከብራቸለሁ። ስራቸውን ለማቃለል ግን በድርጅቱ ላይ ከላይ የተዘረዘረውን ችግር የፈጸሙ ወገኖች በንጹህ ልብ ጥፋታቸውን አምነው ለሽማግሌዎችም ሆነ ለሌሎች ወገኖች በር ካልከፈቱ ሽምግልናውን ለማካሄድ እጅግ ከባድ እንደሚሆን አልጠራጠርም ። የሆነውም እሱ ነው። እርቅ፣ እምነትና ሽምግልና አብረው የሚሔዱ ናቸው። በሽማግሌዎች አማካይነት እርቅ የሚዳርግበት ዋናው ምክንያት በሁለቱ ወገኖች መካከል የችግሩ ምንጭ በሆነው ጉዳይ ላይ ስምምነት ተደርሶ መተማመንን ለመፍጠር ነው። ኢሕአፓን እርቅ በመጠየቅ ላይ ካሉት ግለሰቦች ውስጥ ከሀዲዎች፣ በድርጅቱ ታሪክ ላይ ሽሚያ የሚያካሄዱ አንጃዎች፣ ከወያኔና ከሌሎች የአገሪቱ ጠላቶች ጋር የሚሰሩ ሰላዮች ፣ ድርጅቱን ለማፍረስ ህልም ያላቸው አሉ። አነዚህ ሰዎች ሳይለዩ ሽምግልናው አይሳካም ፤ ከንቱ ሙከራ ነው። ስለሆነም ነው የሽምግልናው ጥረት ሳይሳካ የቀረው። አሁን የበግ ለምድ ለባሾቹ ተኩላዎች ድብቅ ዓላማቸው ግልፅ ሆኖ በለመዱበት የወያኔ መገልገያ ሬዲዮ ጣቢያና ድረገጾች መግለጫ መስጠት ጀምረዋል። ትርፉ ኪሳራና ክስረት ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ማታለል አይቻልም።

ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሆነው በነሐሴ 10 ቀን 2006 ዓ.ም (August 16, 2014) የታሪክ ሽሚያ በማድረግ አበራሽ በርታ በሚል ስም የውይይት መድረክ (Paltalk room) ከፍተው የድርጅቱን 42ኛ ምስረታ በዓል አከበርን ማለታቸውና በእንግድነት ያቀረቡት ግለሰቦች ማንነት ጉዳይና የሰጡት አስተያየት ነው። አቶ ክፍሉ ታደሰ፣ ዶ/ር መላኩ ተገኝና አቶ መሀሪ ረዳ በድርጅቱ አመራር ላይ የነበሩ ግን በድርጅቱ ላይ በፈጸሙት ጥፋት ድርጅቱን ለቀው የወጡ ናቸው። አቶ መሀሪ ረዳ ደግም ወደ ድርጅቱ ተመልሶ አመራር ሆኖ እንደገና ድርጅቱን ለማፍረስ የተንቀሳቀሰ ግለሰብ ነው።አሁን ተመልሶ ሺ ጊዜ መተባበር ያስፈልጋል ቢል ማን ያምናዋል? በውይይቱ ወቅት አቶ ክፍሉ ታደሰ አዲስ ኢሕአፓ ይመሰርት በማለት ቀደም ብሎ ይዞት የነበረውን አቋም አሁንም ደግሞ ውስጥ ውስጡን ከአዲሱ አንጃ መሪ ጋር በመሆን ድርጅቱን ለማፍረስ ያለውን ህልም ገልጿል ፣በወጣቶች መተከት አለበት በማለትም አገርና ሕዝብን ወያኔን ከመሰለ ደመኛ ጠላት ለማለቀቅ በሚደረገው ትግል ላይ የትውልድ ክፍተትን( ወጣትና ወጣት ያልሆን) የሚፈጥር አስተያየት አቅርቧል፣ የድርጅቱን ሁኔታ በሩቁ እከታተላለው ፤ እሳማለሁ ብሏል፤ ቀናነት ቢኖድል እንጂ የሚኖረው ለድርጅቱ አስተየየትና ሀሳብ መስጣት፣ ምክር መለገስ... ወዘተ ማድረግ በሚችልበት አካባቢ ነው። ዶ/ር መላኩ ተገኝ ደግሞ አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት አጠቃላይ ሁኔታ ተጠንቶ አዲስ ድርጅት የሚፈጠርበት ሁኔታ መፈለግ አለበት ብለዋል ። የሁለቱ አስተያየት ተመሳሳይ ነው አዲስ ኢሕአፓ ይመሰርት ነው። በአሁኑ ወቅት በድርጅቱ ዙሪያ ላይ እየተሰራ ያለው ትልቁ ሴራ ግልጽ እየሆነ ነው ። የእነዚህ ግለሰቦች ዋናው ትኩረት ለድርጅቱ ያሰቡ መስለው ለድርጅቱ ቅን አመለካከት ያላቸውን አባላት ከድርጅቱ በመነጠልና በማሳሳት ድርጅቱን ማዳከምና ማፍረስ ነው። በእነዚህ ግለሰቦች የተላለፈው መልዕክት ያለውን ኢሕአፓ አፍርሳችሁ አዲስ ኢሕአፓ መስርቱ ነው። በእነዚህ ግለሰቦች የሚዘወረው እርቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ላይ ያለው የአንጃ ቡዱን ቁንጮዎቹ ዓላማም ይህ ነው። እርቅ የሚሉትም ማታለያ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ደባውን ተገንዝቦ ጉዳዩን በጥንቃቄ መከታተል ያስፈልጋዋል። ስንት ጊዜ ጥፋት የፈጸሙ ሰዎች ስህተታቸውን ሳያምኑ ሕዝብን ያታልላሉ። መቆምና ማስቆም ያለብን ጉዳይ ነው ብዬ አምናለሁ። ያ እርምጃ ካለመወሰዱ የተነሳ ትላንት ደርግና ኢሰፓ ውስጥ ሆነው ኢትዮጵያ አሁን ላላችበት ሁኔታ ያዳረሱ ነፍሰገዳዮች፣ ሕብረትንና ቅንጅትን ያፈረሱ ግለሰቦች፣ በወያኔ መንግሥት ውስጥ ሆነው በሀገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ወንጀል የፈጸሙ ወንጀለኞች በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ተሰግስገው የተቃዋሚዎች ሕብረት እንዳይፈጠር፣ ወያኔ ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዳይወሰድ በማድረግ ትግሉን እየጎዱ ወያኔን እየጠቀሙ ናቸው።

ወደ ርዕሴ ልመለስና እርቅ በዚህ መልኩ የሚካሄድ አይደለም። እውነትን መሰረት ያላደረገ ሽምግልናም ውጤት የለውም። መተማመንም በፍጹም ሊመጣ አይችልም። የለበጣ እርቅ እያሉ ሕዝቡን ውዝንብር ውስጥ ከመክተት አርፎ መቀመጡ የሚሻል ይመስለኛል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ማክበር ያስፈልጋል። የልቡን በልቡ ይዞ ያለና አዋቂ ሕዝብ ነው። ከትዝብት ለማዳን ጥንቃቄ ማድረጉም ጥሩ ነው። ኢሕአፓ ድርጅት ነው። ድርጅቱን ለማፍረስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያዳረጉት፣ከወያኔና ከኢትዮያ ጠላቶች ጋር በመበር በኢትዮጵያ ላይ ትልቅ ጉዳት ያዳረሱት ባንዳዎች የሚሰበሰቡበት ክፍት በረት አይደለም። ስለዚህ በአሁኑ ወቅት በድርጅቱ ዙሪያ ላይ አዛኝና አስታራቂ መስለው የሚቀርቡትን ግለሰቦችና ሁሉንም እንቅስቃሴዎች በጥንቃቄ መመርመር እንዳለበት እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ የግል አስተያየቴንና ምክር መስጠት እፈልጋለሁ። በእጃቸው የንጽሃን ኢትዮያውያን ደም ያላባቸው፣ የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች፣ ሰላዮች፣ ባንዳዎችና አንጃዎች በዚሕ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ላይ ሴራ ከመጎንጎን ስለማይታቀቡ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህን ድርጅት እንድ ዕይን ብሌኑ እንዲጠብቅም ላስገናዝብ እውዳለሁ።

በአጠቃላይ እርቅ፣ እምነትና ሽምግልና አብረው የሚሔዱ ናቸው፤ በአንዳቸው ላይ ሳንካ የሚፈጥር ነገር ከተገኘ ጉዳዩ ሁሉ ዋጋ አይኖረውም። በተለይ ሽማግሌዎች እውነቱን ለመመርመር ብቃት ካጡና ላንዱ ወገን ካዳሉ ማስታረቁ እውን መሆኑ ቀርቶ የበለጠ ጥላቻ እንዲሰፍን ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ጸንታ ትኖራለች!!

ኢሕአፓ አንድ ነው ከፋፋዮች አደብ ግዙ!!